# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
# Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

(አንድነት/United)

ታህሣሥ 6 ቀን 2008 ዓ. ም
December 16, 2015

## ባለቤት የሌላት አገር መከራ አርግዛለች

የአገራችን ዳር ድንበር ለዘመናት ታፍሮና ተከብሮ የኖረው ለአገርና ለሕዝብ ታላቅ አክብሮት በነበራቸውና የአገራቸውንና የሕዝባቸውን ታሪክ ጠንቅቀው በተገነዘቡ አባቶቻችንና እናቶቻችን ከፍተኛ ተጋድሎ ነበር። ኢትዮጵያ አገራችን በታሪኳ አያሌ የውጭ ወራሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ደንበሯን በመድፈር ቅኝ-ግዛታቸው ለማድረግ ተደጋጋሚ ሙከራዎች እንዳደረጉባት በታሪክ የተዘገበ ነው። በተለያዩ ወቅቶች በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ቱርኮች፣ ግብፆች በኋላም ጣሊያኖች ያደረጓቸው ወረራዎች በቆራጥ ሕዝቦቿና በብልህ መሪዎቿ ድባቅ ተመተዋል። በምሥራቁ ክፍል-አገራችንም ቱርኮች፣ ግብፆች፣ በኋላም በአንዳንድ ኃያላን አገሮች ግፊት ሱማሌዎች ከፍተኛ የወረራ ሙከራ አድረገው አልተሳካላቸውም። በምዕራብም እንደዚሁ ሱዳኖች በተለያዩ ጊዜያት ብዙ ወረራዎችን አድርገው ሙከራዎቻቸው ሁሉ ወበከንቱ ሆነው ቀርተዋል። በታሪካችን ፊታኝ በሆኑ ወቅቶች ከነበሩት ታላላቅ መሪዎች አንዱ የሆኑት አፄ ዮሐንስ ሕይወታቸውን ያጡትም ድንበራቸውን ለማስከበር ከደርቡሾች ጋር ባደረጉት የትንቅንቅ ጦርነት ነው። ስለዚህም ነው የአገራችን ዳር ድንበር ተከብሮ የኖረው በቆራጥ አባቶቻችን ደምና አጥንት ነው የምንለው። ለዚህም ነው ኢትዮጵያውያን የምንኖረው ሕይወትና ደም የተገበረለት ሕይወት ነው የሚባለው። ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ከቆየው አፈ-ታሪክ እንደምንገነዘበው የኢትዮጵያ እውቅ መሪዎች አንዱ አፄ ቴዎድሮስ፤ የውጭ አገር ሰዎች ኢትዮጵያን ጎብኝተው ሲመለሱ አፈራችንን በረገጡት ጫማ ይዘው እንዳይሄዱ መሬታችን ለቀው ከመሻገራቸው በፊት እግራቸውን ታጥበው እንዲወጡ ያስደርጉ ነበር ይባላል። እውነትነቱን ልንጠራጠረው አንችልም ምክንያቱም፣ ለሀገርና ለሕዝብ የነበራቸው አክብሮትና ፍቅር እጅግ ከፍ ያለ ነበርና።

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078
Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

ከምዕራቡ ሰሜን ጫፍ የአገራችን ክፍል እስከ ወለጋ ድረስ ባለው ሰፊ ክልል አገር ደንበሩን አስከብሮ የኖረው ሕዝቡ ማለትም በእርሻ ሥራ ላይ ተሰማርተው የኖሩት ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል። በአሁኑ ሰዓትም እንዲሁ ዘብ የቆሙት እነሱው ናቸው። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ለዘመናት መስዋዕትነት የተከፈለበትን ድንበራችንን ማለትም የአትባራና የሰቲት ውኃ የሚፈስበትን ርዝመቱ 1300 ኪሎ ሜትር ስፋቱ ደግሞ ከ20 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሆነውን ለም መሬታችንን ለሱዳን ቆርሶ ለመስጠት ዝግጅት ላይ መሆኑን ህወሓት/ኢህአዴግ በሚስጢር ለመያዝ ቢሞክርም፣ የሱዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ ከማል አላዲን እስማኤል፤ ይፋ አድርጎታል።

ይህንን ሀገራዊ ጉዳይ የሱዳን መንግሥት ለራሱ ሕዝብና ለዓለምአቀፉ ኅብረተሰብ ይፋ እያደረገ ባለበት በአሁኑ ሰዓት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ተብየው ግን እንኳን ለሕዝብ ይፋ ሊያደርግ ቀርቶ፣ የሕዝብ ተወካይ ብሎ ለሰየመው አሻንጉሊት ፓርላማ እንኳን አቅርቦ አላወያየም። አገርን ያህል ነገር በድብቅ የሚቸረችርን ቡድን መንግሥት ነው ብሎ መቀበል ይቻላልን? የኢትዮጵያ ገበሬዎች ወደ ሱዳን ገብተው ሲያርሱት የኖሩት መሬት የኔ ስለሆነ ሊመለስልኝ ይገባል እያለች ሱዳን የምታምታታው ድሮ እንግሊዝ የቅኝ ግዛቷን ለማስፋት ከሱዳን አልፋ ወደ ኢትዮጵያ መሬት በመግባት የያዘችው መሆኑ የታወቀ ነው። ይህንን የ1908 ዓ. ም የእንግሊዝን መሰሪ ተንኮል የአገራችን መንግሥታት በአፄ ምኒልክ፣ በአፄ ኃይለሥላሴም ሆነ በደርግ ጊዜ ከቶውንም ተቀብለውት አያውቁም፤ እንዲያውም በወቅቱ የነበሩት የአገር መሪዎች የኢትዮጵያ መሬት ወደ ሱዳን ተውስዶብናል እያሉ ሲከራከሩ ያልኖሩትን ያህል፣ ዛሬ ይህ ኃላፊነት የጎደለው የህወሓት አገዛዝ ድንበራችንን ቆርሶ በድብቅ አሳልፎ ሊሰጥ ቀነ-ቀጠሮ መያዙ በእጅጉ የሚያሳዝን የአገር ውርደትና የታሪክ ጠባሳ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሱዳን ኤምባሲ አሁን በቅርቡ በሰጠው ቃለ-መጠይቅ፣ “በአፄ ኃይለሥላሴ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሥ ጡረታ የወጡ ወታደሮቹን ሱዳን መሬት ላይ በማኅበር እያረሱ እንዲኖሩ አድርጎ ስለነበር፣ በጊዜው ግጭት ውስጥ ላለመግባት ወስነን ቆይተናል፣ አሁን የምናስመልሰው ያንን መሬታችንን ነው” ይላል። በንጉሠ ነገሥቱ ጊዜ የወታደሮች አክሲዮን የእርሻ ማኅበር የነበረውን አብደራፊን መሆኑ ነው።

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009
Phone: 202- 241 2078
Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com

ህወሓት/ኢህአዴግ ድንበር ማስከበር ይቅርና በየጠረፉ ያሉ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎች ድንበር ዘለሉን የሱዳን ገበሬና የወታደር ካምፑን አስነቅለው ሲያባርሩት የራሱን ገበሬዎች በአጥፊነት የሚወነጅለውና የሚቀጣው የአማራ ክልል መንግሥት ተብዬው ሆኗል።

ህወሓት/ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ ለዘመናት ተቻችሎና ተከባብሮ የኖረውን ሕዝባችንን በጎሣ ከልሎ ልዩነትን በማራገብ እርስ በርስ እያናቆረ ለወደፊቱ ሕዝባችን በአገሩ አብሮ እንደዱሮው ተዋዶና ተከባብሮ ከማይኖርበት ደረጃ ላይ እያደረሰው ነው። በህወሓት/ኢህአዴግ የሥልጣን ዘመን በጎሳሣ ግጭት ምክንያት ሕዝብ ከቀየው ያልተፈናቀለበትና የሰው ሕይወት ያልጠፋበት አካባቢ የለም ማለት ይቻላል። በተጨማሪም በሁለት ጎሣዎች መካከል የድንበር ግጭት ሲነሳ፤ የህወሓት የፌደራል ወታደር ጣልቃ እየገባ ሕዝብን ከሕዝብ ያጨፋጭፋል። ሕዝብ ተወልዶ ካደገበት ቦታ ዘራችሁ ከዚህ ክልል ባለመሆኑ፣ አማራ የሆናችሁ ወደአማራ ክልል፣ ኦሮሞ የሆናችሁ ወደ ኦሮሞ ክልል...ወዘተ መሄድ አለባችሁ እያለ የአካባቢውን ኗሪ በማነሳሳትና በማጋጨት የሕዝብ ደም በከንቱ እንዲፈስና ሕዝቡም ደም እንዲቃባ እያደረገ ነው። በተለይ አማርኛ ተናጋሪውን ሕዝብ ከኢትዮጵያ መሬት ነቅሎ ለመጣል ወይም ለማጥፋት ከፍተኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል እየፈጸመበት ይገኛል። ለምሳሌ በስልጤ ክልል ውስጥ ተውልደውና ተጋብተው የኖሩ አማርኛ ተናጋሪዎች ስልጤን ለቃችሁ ውጡ በመባላቸው መንግሥት ያለ መስሏቸው አቤቱታ ሊያሰሙ ቢሄዱ፣ የህወሓት ካድሬዎች "የአማራና የውሻ ጩኸት መስማት አንፈልግም" የሚል መልስ ሰጥተዋቸዋል። አሁን በቅርቡም በምዕራብ ጎጃም፤ በቀድሞው የመተከል አውራጃ (በአሁኑ አጠራር የቤኒሻንጉል ክልል) ሰዎች ለዘመናት ከኖሩበት ቀየ በህወሓት/ኢህአዴግ ካድሬዎች ቀስቃሽነት ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆኑ አማርኛ ተናጋሪዎች አሰቃቂ ጭፍጨፋ ደርሶባቸዋል። ስሞኑን ደግሞ በጎንደር ዙሪያ፣ በላይ አርማጭሆ ወረዳ ልዩ ስሙ ጋባ ጋላገር ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሕዝቡ በሰላም አርሶ ከሚኖርበት ቀየ ድረስ ህወሓት ወታደሮቹን በመላክ አርሶ አደሩን ትጥቅ ለማስፈታት በአደረገው ሙከራ ጦርነት ተነስቶ በርካታ የሰው ሕይወት ጠፍቷል። ዕኩይ ድርጊቱ የማያልቅበት ህወሓት በዚህ አካባቢ አንድ ዓይነት ኃይማኖት፣ ባህልና ወግ ባለው ሕዝብ መካከል ቅማንትና አማራ የሚል ድንበር ከልሎ ለማፋጀት ከፍተኛ የካድሬ ቅስቀሳ ያደረገ ቢሆንም፣ ሕዝቡ በአንድ ቃል ችግራችን

ከአማራው የክልል አገዛዝ ጋር እንጂ ከወገናችን ከአማራው ሕዝብ ጋር አይደለም በማለት ጠንካራ አቋሙን ግልጽ አድርጓል።

ከዚህ ቀደም ያለ ሕዝብ ውሳኔ ኤርትራን ለሻቢያ አሳልፎ የሰጠ አምባገነን አገዛዝ አሁን ደግሞ ለም መሬታችንን ለሱዳን ቁርሶ ለመስጠት እንዲያስችለው ሕዝብን ከሕዝብ በማባላት ታሪካዊ የአንድነት ኃይላችንን እየሸረሸረ ስለሆነ ይህንን ተንኮል ሕዝብና ተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ በአንድነት ቆመው የመታገል አገራዊ ግዴት አላለባቸው። ሕዝቡ ሁኔታው አንገሽግሾት በየቦታው በህወሓት/ኢ.ህአዴግ ላይ እያሳየ ያለው መነሳሳት ሊበረታታና ሊቀነባበር የሚገባው እንቅስቃሴ በመሆኑ፣ ማንኛውም ህወሓት/ኢ.ህአዴግን የሚቃወም የፖለቲካ ድርጅት፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ አገር ወዳድ ግለሰቦችና ምሁራን እጅ ለእጅ ተያይዘው በአንድ ላይ በመቆም ለአገርና ለወገን በሚበጅ ጉዳይ ላይ ከልብ መምከር ያለባቸው ጊዜ አሁንና አሁን ነው። ከተለያዩ አገሮች ተመክሮዎች በመማር ብሔራዊ አመለካከትን በማጎልበት የአገር ወዳድ ግለሰቦችን፣ የማኅበረሰቦችንና የፖለቲካ ድርጅቶችን ስብስብ እያጠናከርንና፣ እየተቻቻልን ከአባቶቻችንና ከቅድመ-አያቶቻችን የተረከብነውን ዳር-ድንበር ለተተኪው ትውልድ ማስረከብ ታሪካዊ ግዴታችን ነው። ለዚህም የኢ.ሕአፓ (አንድነት) ምንጊዜም ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን የቆመ መሆኑን ያረጋግጣል!

የኢ.ሕአፓ (አንድነት) የህወሓት/ኢ.ህአዴግ አገዛዝ ከሕዝብ ተደብቆ የአገራችን ለም መሬት ቁርሶ ለሱዳን ሊሰጥ እያደረገ ያለውን ስምምነት በጥብቅ ያወግዛል! መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚደረገውን ስምምነት አልቀበልም እንዲልና የህወሓት/ኢ.ህአዴግን አገዛዝ በአንድነት ቆሞ እንዲታገል ጥሪያችንን እናቀርባለን!

ኢትዮጵያ ለዘላለም በነፃነት ትኑር!

**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**
**Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**